የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፮
አዲስ አበባ መጋቢት ፩ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No.26
ADDIS ABABA 10th March, 2017

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፱፻፺፰/፪ሺ፱ ዓ.ም

ለመቀሌ-ዳሎል እና ሠመራ-አፍዴራ የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከአፍሪካ ልማት ባንክ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ………ገጽ ፱ሺ፭፻፸፬

**Contetes**

Proclamation No.998/2017

African Development Bank Loan Agreement for the Mekelle-Dallol and Semera-Afdera Power Supply for Industrial Development and Access Scale-up Project, Ratification Proclamation ……………………………..………….. --Page 9574

## አዋጅ ቁጥር ፱፻፺፰/፪ሺ፱

## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአፍሪካ ልማት ባንክ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለመቀሌ-ዳሎል እና ሠመራ-አፍዴራ የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፩፻፬ ሚሊዮን ፮፻፲ ሺ (አንድ መቶ አራት ሚሊዮን ስድስት መቶ አሥር ሺ) የአሜሪካን ዶላር የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአፍሪካ ልማት ባንክ መካከል እ.አ.አ ሴፕቴምበር ፩ ቀን ፪ሺ፲፮ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥር ፴ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION NO. 998/2017

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE AFRICAN DEVELOPMENT BANK

WHEREAS, a Loan Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Bank stipulating that the African Development Bank provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan in an amount not exceeding 104,610,000.00 (One Hundred and Four million Six Hundred and Ten Thousand) United States Dollars for financing the Mekelle-Dallol and Semera-Afdera Power Supply for Industrial Development and Access Scale-up Project, was signed on 1st day of September, 2016;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 7th day of February, 2017;

NOW,THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "ለመቀሌ-ዳሎል እና ሠመራ-አፍዴራ የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከአፍሪካ ልማት ባንክ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፺፰/፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአፍሪካ ልማት ባንክ መካከል እ.አ.አ ሴፕቴምበር ፩ ቀን ፪ሺ፲፮ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 2000200000253 በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፩፻፬ ሚሊዮን ፮፻፲ ሺ (አንድ መቶ አራት ሚሊዮን ስድስት መቶ አሥር ሺ) የአሜሪካን ዶላር በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት ፩ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "African Development Bank Loan Agreement for the Mekelle-Dallol and Semera-Afdera Power Supply for Industrial Development and Access Scale-up Project, Ratification Proclamation No. 998/2017"

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Loan Agreement Number 2000200000253 signed on the 1st day of September, 2016; between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Bank is hereby ratified.

**3. <u>Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation</u>**

The Ministry of Finance and Economic Cooperation is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of 104,610,000.00 (One Hundred and Four million Six Hundred and Ten Thousand) United States Dollars in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done At Addis Ababa, this 10th Day of March, 2017.**

**MULATU TESHOME (Dr.)**

**PRESIDANT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**